ሴፕቴምበር 5/2018 ፈጣን መልእክት/QuickNotes

**የ2018-2019 የትምህርት ዓመት ታላቅ አጀማመር**

ማክሰኞ ሴፕቴምበር 4፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የ2018-2019 ን የትምህርት ዓመት በታሪኩ የመጀመሪያ የሆነውን ከ163,500 በላይ ተማሪዎችን እንኳን ደህና መጣችሁ በማለት በሩን ክፍቶ ተቀብሏል።

የ2018-2019 የትምህርት ዓመት በታላቅ ድምቀት የተጀመረው ማክሰኞ ሴፕቴምበር 4 የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ከበፊት ይልቅ ቁጥራቸው ከፍተኛ ለሆኑ ተማሪዎች በሩን ክፍት በማድረግ ነው። በዚህ ዓመት ዲስትሪክቱ ባሉት 206 ት/ቤቶች ውስጥ ከ 163,500 በላይ ተማሪዎች እንደሚከታተሉ የሚጠበቅ ሲሆን ይህም ከ 2017-2018 የትምህርት ዓመት ከ 1,000 በላይ የተማሪዎች ቁጥር ጭማሪ አሳይቷል።

ዲስትሪክቱ በተጨማሪ በዚህ የትምህርት ዓመት 900 አዳዲስ መምህራን፣ ከ250 በላይ የድጋፍ አገልግሎት ባለሙያዎችን፣ እና 25 አዳዲስ አስተዳዳሪዎችን ተቀብሏል።

እያደገ የመጣውን ት/ቤት የመግባት ሁኔታ ለማስተናገድ፣ሮክቪል (Rockville) የሚገኘው የ ባያርድ ረስቲን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት (Bayard Rustin Elementary School) ከ K–5 ከ600 በላይ ተማሪዎችን ለመቀበል በር ከፍቷል። በተጨማሪም እያደገ የመጣውን የትምህርት ምዝገባ ለመቀበል/ለማስተናገድ የቤተዝዳ-ቼቪ ቼዝ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Bethesda-Chevy Chase High School)፣ ኖርዝ ቤተዝዳ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት (North Bethesda Middle School)፣ እና ከንሲንግተን ፓርክውድ (Kensington Parkwood) እና ሉሲ ቪ. ባርንስለይ አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች (Lucy V. Barnsley elementary schools) ተስፋፍተዋል።

ለአዲሱ የትምህርት ዓመት የሞንትጎመሪ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በተለያዩ ፕሮግራሞች ላይ ለሁሉም ተማሪዎች የትምህርት ዕድል ለማሻሻል/ለማሳደግ የማስተማሪያ ጊዜ ለማስፋት ቁልፍ ፋይዳ ባላቸው ፕሮግራሞች ላይ የትምህርት ሠዓትን ለመጨመር ኢንቨስት አድርጓል። እነኚህ ወሳኝነት ያላቸው ፋይዳዎች ቋንቋ እና የምንባብ/መሠረታዊ ትምህርት የማዳበር እድሎችን ማስፋት፤ በቀደምትነት ትምህርት መጀመር፤ ለጠንካራ የኮርስ ሥራዎች እና ምዘና/ፈተናዎች ተደራሽነትን ማስፋት/መጨመር፤ እና ለሥራ ዝግጁነት ላይ ትኩረት ማድረግን ያካትታሉ።

ወላጆች እና ተማሪዎች የት/ቤት መጀመሪያ ቀን ፎተግራፎች የሚወዱትን እንዲልኩልን ተጋብዘው ነበር። MCPS ደርዘኖችን/ብዙ የተላኩለትን አግኝቷል፤የመጀመሪያ ቀን ፎተግራፎች ማሳያ/ማዕከለ ስዕላት ይመልከቱ እዚህ።

ይበልጥ ይወቁ

**ለሁሉም ተማሪዎች ሠላማዊና ደስ የሚያሰኝ ት/ቤት መፍጠር**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለሁሉም ተማሪዎች እና ሠራተኞች ሠላማዊና ደህንነት የሠፈነበት የትምህርት አካባቢ ለማቅረብ በቁርጠኝነት ይሠራል።

አዲሱ የትምህርት ዓመት ተጀምሯል እናም የሠላምና የፀጥታ/ደህንነት ጉዳይ በብዙዎቻችሁ አእምሮ እንደሚመላለስ እናውቃለን። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ዋና ዓላማ እንደ ት/ቤት ስርአት ሁሉንም ተማሪዎች ለወደፊታቸው መሻሻል ለማብቃት እያዘጋጃቸው ቢሆንም፣ ተማሪዎች ደህንነታቸው የተጠበቀ እና በትም/ቤት ተቀባይነት ካላገኙ ይህ ሊደረስበት አይቻልም።

የአውቶቡስ እና የህንፃ ደህንነትና ሠላምን ጨምሮ፣ የልጅ ማጎሳቀል፣ ማስጨነቅ/ወከባ እና ራስን መግደል መከላከል፣ እና የአካባቢ ደህንነትን በመንከባከብ ሠላማዊ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የትምህርት አካባቢ ለማቅረብ MCPS ሁለገብ ዘዴዎችን ይጠቀማል።

ዲስትሪክቱ የተማሪዎችን ደህንነት ለመጠበቅ ከሚወስዳቸው እርምጃዎች መካከል ከዚህ በታች ያሉት ጥቂቶቹ ናቸው:-

**የህንፃ እና የአውቶቡስ ደህንነት**

- በት/ቤቶች ላይ መቆጣጠሪያ ያላቸው የመግቢያ በር ሲስተም
- በእያንዳንዱ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የት/ቤት ደህንነት ጥበቃ መኮንን የበለጠ ያንብቡ
- በስቴት እና አገር አቀፍ የጾታ ጥቃት ያደረሱ ከመረጃ ቋት/databases ዉስጥ ጎብኚዎችን የሚፈትሽ በት/ቤቶች የጎብኚዎች ማኔጅመንት አሠራር

- ለእያንዳዱ ት/ቤት ወቅታዊ የሆነ የድንገተኛ/የአጣዳፊ ዝግጁነት እቅዶች የበለጠ ይወቁ
- በጠቅላላ በካውንቲው የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶችን፣ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶችን፣ እና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችን የሚረዱ በመቶዎች የሚቆጠሩ ለዓላማቸው የቆሙ የMCPS ሰኩሪቲ/የጥበቃ ሠራተኞች
- ስለ ት/ቤት ሠላም እና ደህንነት ሁለገብ ሪፖርት የ2018 ሪፖርት እና የሥራ እቅድ ያንብቡ
- በዚህ ዓመት በአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶችም እየተጨመሩ ካሉት ካሜራዎች ጋር፣ በሁሉም የሁለተኛ ደረጃ እና የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሰኩሪቲ ካሜራዎች
- በአብዛኛዎቹ አውቶቡሶች የውስጥ እና የውጭ ካሜራዎች፣ እስከ ትምህርት ዓመቱ መጨረሻ ድረስ በሁሉም አውቶቡሶች ላይ የሚገጠሙትን ካሜራዎች ጨምሮ "Respect the Bus" የተሰኘውን ቪድዮ ይመልከቱ
- በህንፃዎች ደህንነት ላይ የሁሉም የሥራ ባልደረቦች ቅኝት/ንቁነት እና ትኩረት
- የእግረኛ ደህንነት ሪሶርሰስ (የበለጠ ይወቁ)

**የልጅ/ህፃን ጉስቁልናን መከላከል**

- ለሁሉም ሠራተኞች፣ ኮንትራክተሮች፣ እና አንዳንድ በጎ ፈቃደኞች ዘርፈ-ብዙ የበፊት ታሪካቸውን ማጣራት ይበልጥ ለማወቅ
- ለሠራተኞች፣ ለኮንትራክተሮች እና ለበጎ ፈቃደኞች ስለ ልጆች መጎሣቆል እና ቸልተኝነትን መከላከል፣ ማጤን እና ሪፖርት ስለማድረግ ግዴታዊ የሆነ ስልጠና ይሰጣል ስልጠና ይውሰዱ
- ከእድሜ-እና ከእድገት ጋር ተገቢ የሆነ የግል ሰውነትን ደህንነት ስለመጠበቅ ለሁሉም ተማሪዎች ትምህርት ይሰጣል ትምህርቶቹን ይመልከቱ
- ማጎሳቆል እና የጥቃት ተግባርን ሪፖርት ስለማድረግ የተቀናጀ ሂደት (ስለ ህፃን/ልጅ ማጎሳቆል የእኛን የ MCPS የሪፖርት አደራረግ ፖሊሲ ይመልከቱ)
- ለሁሉም ሠራተኞች የስነምግባር ደንብ የበለጠ ያንብቡ

**የማስጨነቅ/ማንገላታት እና የማስፈራራት መከላከል**

- ጥቃት/ማስጨነቅ/ወከባ ሲያጋጥም የተቀናጀ የሪፖርት አቀራረብ ሂደት (ጥቃት ሲሰነዘር ሪፖርት ማድረግያ ቅጽ)
- ስለ ማስጨነቅ/ማንገላታት፣ ማስገደድ፣ እና ማስፈራራት መከላከል እና ሪፖርት ስለማድረግ ለሁሉም ሠራተኞች ስልጠና መስጠት
- ለተማሪዎች ስለ ዲጂታል ሲትዝንሽፕ እና ሳይበርቡሊንግ ማስጨነቅ፣ ማስፈራራትን መፋለም/combatting cyberbullying and harassment ትምህርት መስጠት የበለጠ ይማሩ
- ስለ ተማሪ የጾታ ማንነት ጉዳዮችን የሚመለከት መመሪያ (የበለጠ ያንብቡ)
- ለተማሪዎች የካውንስሊንግ/የምክር ድጋፍ

- የኃይማኖት ልዩነቶችን ስለ ማክበር መመሪያ (መመሪያዎቹን ያንብቡ)
- ፖሊሲ/Policy ACA፡- አድሎ የሌለበት፣ እኩልነት/ፍትሃዊነት፣ እና የዳበረ ባህል (ፖሊሲውን ያንብቡት )
- አክብሮትን ይምረጡ የልጆች ጤናማ የፍቅር ግንኙነት ዓመታዊ ኮንፈረንስ የበለጠ ይማሩ

**የአእምሮ ጤንነት እና ደህንነት**

- ለሁሉም የመካከለኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ተማሪዎች ራስን ስለማጥፋት የመከላከል ስልጠና
- BtheOne ስለ አእምሮ ጤንነት ቅስቀሳ-ዘመቻ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ጋር በመተባበር፣ Every Mind and Family Services, Inc. ስለ ቅስቀሳው ይማሩ
- በሁሉም ደረጃዎች ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች ሁለገብ የጤና ሥርዓተ ትምህርት/ከሪኩለም
- የአእምሮ ጤንነት ሪሶርሶች እና ለቀውስ ሁኔታ ለተማሪዎች የሚደረጉ ድጋፎች የበለጠ ይወቁ
- ራስን መግደል ስለመከላከል እና ጣልቃ ገብነት ለሁሉም ሠራተኞች ግዴታ የሆነ ስልጠና
- ራስን የመግደል ስጋትን ሪፖርት ማድረጊያ የተሻሻለ/የተቀናጀ አሠራር-ሂደት የበለጠ ያንብቡ
- ለትምህርት ተነሳሽነት አገናኝ የበለጠ ያንብቡ
- ከሱሰኝነት ለተላቀቁ ተማሪዎች የማገገሚያ አካደሚክ ፕሮግራም የበለጠ ይወቁ
- ለሞንትጎመሪ ካውንቲ የአደንዛዥ እፅ መጥፎ አጠቃቀም ግምገማ እና ህክምና መጠቀሚያዎች/Resources መጠቀሚያዎችን ይመልከቱ
- ለሠራተኞች ስለ ስነምግባር አስጊ ሁኔታ ስልጠና መስጠት
- ለተማሪዎች ፍትሃዊ የተሃድሶ ፕሮግራሞች የበለጠ ይወቁ

**የአካባቢ ደህንነት**

- የመጠጥ ውኃ ምርመራ የበለጠ ይወቁ
- ከእሳት አደጋ መጠበቅ
- የመጫወቻ ሜዳ ደህንነት የበለጠ ያንብቡ
- ራዶን ምርመራ/Radon testing ሪፖርቶችን ይመልከቱ

**ታላቅ እና ሠላማዊ የትምህርት ዓመት ይሁንላችሁ!**

**በትምህርት የቤት ስራ/Homework እርዳታ ትፈልጋላችሁ ወይ? ነፃ የቤት ስራ እርዳታ እዚህ ይገኛል!**

አዲሱ የ "Homework Hotline Live!" ወቅት ረቡእ፣ ሴፕቴምበር 5 በአውታረ-መረብ የትምህርት የቤት ሥራ ይጀመራል። የቴሌቪዥን ፕሮግራም/TV program ማክሰኞ፣

ሴፕቴምበር 25 ይጀመራል። ተማሪዎች ፕሮግራሙ እየተላለፈ ባለበት ሠዓት መደወል ይችላሉ ወይም ጥያቄዎቻቸውን ኦን ላይን፣ ቴክስት መልክት ወይም በሶሻል ሚዲያ አማካይነት ለማቅረብ ይችላሉ፣

ለ33 ዓመታት፣ "Homework Hotline Live" (HHL) ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) መምህራን በሚገኝ ከትምህርት-ሰዓት-በኋላ የቤት ስራ ነፃ እገዛ በማቅረብ ከሙአለህፃናት እስከ 12ኛ ክፍል የሚገኙ በሺዎች ለሚቆጠሩ ተማሪዎች እገዛ አድርጓል። HHL አንድ-ለ-አንድ የቤት ሥራ በማሠራት ለመርዳት በሚያስችለው አውታረ-መረብ (the web)፣ ሞባይል አፕ (mobile app)፣ እና ኬብል ቲቪ (cable TV) ይጠቀማል። HHL በቲቪ በሚሰራጭበት ወቅት፣ ተማሪዎች በቲሌፎን ጥያቄዎች በማቅረብ ከመምህራን ጋር አብረው ፕሮብሌሞች ሲሰሩ ማየትና መስማት ይችላሉ።

HHL የ2018-2019 ክፍለጊዜውን መስመር ላይ የቤት ስራ እርዳታ በማቅረብ ሰፕተምበር 5 ይጀምራል። "Homework Hotline Live" ማክሰኞ ሴፕቴምበር 25 በቴሌቪዥን (TV) ከ4:30 – 6 p.m በ MCPS-TV ይጀመራል። ተማሪዎች ለእርዳታ ከማክሰኞ – ሃሙስ ከ4:30 – 6 p.m. ወደ HHL ሊደውሉ ይችላሉ፤ ወይም ከማክሰኞ – ሃሙስ ከ4:30 – 9 p.m፣ እና ሰኞ ከ6 – 9 p.m ጥያቄዎች መስመር ላይ ማቅረብ ይችላሉ። በቴሌቪዥን ስርጭት ወቅት/TV broadcast ጥያቄዎች በሙሉ በአየር ላይ ይመለሳሉ። በሌላ ወቅት የሚቀርቡ ጥያቄዎች መስመር-ላይ መልስ ያገኛሉ።

ነፃ የሆነ"Homework Hotline Live"mobile app ይገኛል ለ Apple iOS እና Android መገልገያዎች! ተማሪዎች "Homework Hotline Live"app ቴሌቪዥን ስርጭት እየተካሄደ ሊከታተሉ/ሊመለከቱ ይችላሉ፣ አንዲት ቁልፍ በመንካት ለትምህርት የቤት ሥራ እርዳታ ለመጠየቅ/ለመደወል፣ ወይም app's "Ask Us" መተግበሪያ በመጠቀም ጥያቄ ለማቅረብ ይችላሉ። ተማሪዎች የቤት ስራ ፕሮብሌማቸውን ፎቶግራፍ ከ"Ask Us" ጥያቄአቸው ጋር ማያያዝ በተጨማሪ ይችላሉ። የHHL መተግበርያ ብዙ የቤት ስራ ማገዣ መሳርያዎችና እገናኞች አሉት።

ተማሪዎች ወደ HHL ለመድረስ ብዙ መንገዶች አሏቸው፦

- ስልክ፡- 301-279-3234
- ድር፡- AskHHL.org
- የHomework Hotline Live/ህያው የቤት ስራ ሆትላይን መተግበርያ
- ፅሁፍ፡- 724-427-5445 (7244-ASK-HHL)
- ኢሜይል፡- question@AskHHL.org

"Homework Hotline Live" ን ከ ሴፕቴምበር 25 ጀምራችሁ በ MCPS-TV ማክሰኞ፣ ሮብ፣ ሐሙስ ከ4:30 – 6 p.m. ተመልከቱ፡-

- ኮምካስት/Comcast 33
- Verizon Fios 35
- RCN 88
- AskHHL.org
- ዩትዩብ/YouTube (AskHHL) ይፈልጉ
- "Homework Hotline Live" app/መተግበርያ

**የቅዳሜ ት/ቤት ተማሪዎችን ስኬታማ እንዲሆኑ ያግዛል።**

**የቅዳሜ ት/ቤት ተብሎ የሚታወቀው የጆርጅ ቢ. ቶማስ ሲንየር የትምህርት አካደሚ** (George B. Thomas, Sr. Learning Academy) **ምዝገባ ተጀምሯል። ሴፕቴምበር 15 የክፍል ትምህርት ይጀመራል።**

**የጆርጅ ቢ. ቶማስ ሲንየር የትምህርት አካደሚ** (George B. Thomas, Sr. Learning Academy) **የ 2018-2019 የቅዳሜ ት/ቤት** Saturday School **ቅዳሜ ሴፕቴምበር 15 ይጀምራል። የቅዳሜ ት/ቤት የ**MCPS **ተማሪዎች የዋነኛ ኣካዴሚያዊ ርእሶች ልቀታቸውን ለማበልፀግ የሚያግዛቸው ባለ-ኣነስተኛ-ዋጋ የቱተር እና ሜንቶር ፕሮግራሞች የሚከናወንበት ስድስተኛዉን የትምህርት ቀን የሚያቀርብ ፕሮግራም ነው። ተጨማሪ ኣካዴሚያዊ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች በ** Montgomery County **ዙሪያ ከሚገኙት 12 ቦታዎች ኣንዱ ላይ ፕሮግራሞችን መከታተል ይችላሉ። ትምህርቶች የሚጀምሩት ቅዳሜ፣ ሴፕት. 15 ነው በሜይ ወርም ያልቃል። የምዝገባ ዋጋ ነፃ እና የቅናሽ ዋጋ ምግብ/**Free and Reduced-price Meals (FARMS) **ለሚቀበሉ $40 ሲሆን** FARMS **ለማይቀበሉ ደግሞ $85 ነው።**

[ጆርጅ ቢ. ቶማስ ሲንየር የትምህርት አካደሚ/George B. Thomas, Sr. Learning Academy]

**ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ** (MCPS) **መረጃዎችን/ኢንፎርሜሽን እንዴት እንደሚያገኙ ለማሻሻል ይርዱን**

እባክዎ እርስዎ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) **መረጃ/**ኢንፎርሜሽን **የሚያገኙበትን** ሁኔታ ዲስትሪክቱ ለማሻሻል ስለሚረዳን ይህንን አጭር ዳሰሳ ይሙሉ።

**ዜና እና መረጃ እንዴት እንዲደርስዎት ይፈልጋሉ? ለእርስዎ አስፈላጊ የሆነው የትኛው የ** MCPS **ዜና/መልእክት ነው? ይህንን ዳሰሳ** ይውሰዱ እና እርስዎ የሚመርጡትን የመገናኛ አውታር

ይንገሩን። እርስዎ የሚሰጡንን ምላሽ እንዴት ከ MCPS መረጃ/ኢንፎርሜሽን ማግኘት እንዳለብዎት ለማሻሻል እንጠቀማለን።

**ስለ ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሥርአተ ትምህርት ለውጦች የበለጠ ይወቁ፦**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለአንደኛ ደረጃ እና ለመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት አዲስ ሥርዓተ ትምህርት እና የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን በመገምገም እና በመምረጥ ሂደት ላይ ነው።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) K–8 የእንግሊዝኛ እና የሂሳብ ሥርዓተ ትምህርት/ከሪኩለም ለውጥ በማድረግ ላይ ነው። ዲስትሪክቱ አዲስ ሥርዓተ ትምህርት እና የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን በመገምገም እና በመምረጥ ሂደት ላይ ነው። በሚቀጥሉት በርካታ ወራት፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ከሠራተኞች፣ ከማህበረሰብ አባላት እና ሌሎች አጋሮች ጋር ስለ መረጣ ሂደቱ ግብረመልሶችን ለመሰብሰብና የመረጣ ሂደት ዋና ሀሳብ/ረቂቅ ላይ ይሠራል።

ወላጆች እና የማህበረሰብ አባላት አጭር ዳሰሳ በመሙላት ጥያቄዎችን ማቅረብ እና አስተያየቶቻቸውን ለማካከፈል ይችላሉ። ስለ ሥርአተ ትምህርት ምርጫ ሂደት መደበኛ ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት እባክዎ ድረ-ገጽ ይጎብኙ።

ከዋና የአካደሚክ/ትምህርት ኃላፊ የተላለፈ መልእክት ያንብቡ